# ዱቼ ሙሶሊኒ! ቻው ፋሽስት ወያኔ

## Mussolini Duce, Ciao Fascimo Woyane

ታሪክ ራሱን ይደግማል የሚለው ተራ ግን ደግሞ እጅግ ጠጣር ጥሬ ሃቅ፤ ባለፈው መነጽር፥ ዛሬንና ነገ ይመጣ ዘንድ ያለውን ያሳየናል። እናም እነሆ የ"ታላቋ" ፋሽስት ጣልያን ኢትዮጵያን የመቆጣጠር ልክፍት ወያኔን በጫካ ትልግ አደቁኖ፣ በሃያ አምስት ዓመታት ግፈኛ አገዛዝ አቀስሶ ኢትዮጵያን ረግጦ እንዲገዛ የከፋፍለህ ግዛ መንፈሱን አውርሶት እንደነበረ ገሃድ እየወጣ ነው። ይኸው ሃቅ፥ ዛሬ በግሎባላይዜሽን የቴክኖሎጂ ዘመን ተመልሶ፥ በኢትዮጵያ ላይ፥ ከኢትዮጵያ በበቀሉ እፉኝቶች ዳግም ይተገበራል ብሎ፥ እንኳን የተነበየ የጠረጠረም አልነበር። ይኸማ ቢሆን ኖሮ በደርግ ቀብር ማግስት የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ወያኔንም፥ ሥር ሳይሰድ፥ ቅርንጫፍ ሳይዘረጋ፥ ከደርግ ጎን ያጋድመው ነበር። ግን ነበር ነው፤ ሃያ አምስት ዓመታት በከንቱ አልፈዋል፤ ዛሬ የተረፈን ቁጭትና ፀፀቱ ብቻ ነው።

ወያኔ ከፈጸማቸው ወደርየለሽ ጭካኔያዊ በደሎች ሁሉ ጎልቶ መታየት ያለበት በመጠራጠርና በአለመተማመን ጭንብል ዓይነ ልቡናችንን ማሳወሩ ነው። "በጨለማ የሄደ ሕዝብ ታላቅ ብርሃን ዐየ" እንዲል መጽሐፍ፥ ይህ የጨማለ መጋረጃ ይገለጣል፣ የጨለማውም የአገዛዝ ሠንሠለት በዚህ ፍጥነት ይበጠሳል ተብሎ በማይጠረጠርበት ቅጽበት፥ የማይሆነው ነገር፥ የሚመስለን፤ ተአምር በሚያሰኝ መልኩ እየሆነ፥ እያየነው መጣ። የብርሃኑን ጭላንጭል ከሩቅ እያየነው ነው።



Figure 1 ከዊኪፔዲያ ገጽ የተወሰደ። ተዘቅዝቆ የተሰቀለው ሙሶሊኒ፥ የግራ ወደ ቀኝ 2ኛው [https://en.wikipedia.org/wiki/Benito_Mussolini#/media/File:Mussolini_e_Petacci_a_Piazzale_Loreto,_1945.jpg](https://en.wikipedia.org/wiki/Benito_Mussolini#/media/File:Mussolini_e_Petacci_a_Piazzale_Loreto,_1945.jpg)

25 ዓመታት ሚሊዮኖች ተረሸኑ፣ ታፍሰው ታጎሩ፣በግርፋትና በኢሰብአዊ ቅጣት ተሠቃዩ፣ እርባና እንደሌለው ዕቃ ከሰብአዊነት በወረደ ደረጃ ተጣሉ፣ ተሰደዱ፣ ልሳናቸው እንዲዘጋ ተደረገ፣ በማንነታቸው ተሰደቡ፣ ተንቋሸሹ፣ ሃድጊ-አህያ፥ ትምክሕተኛ፥ ሸንታም አማራ ተብለው ተዋረዱ። ከፍጡርነት አንሰው በፈጣን ሎተሪ ደረጃ ተመነዘሩ፥ ጠባብ፣ የዋህ (ሞኝ) ኦሮሞ ተብለው ተንጓጠጡ። የእነርሱ ሃብት ሌላውን አለማ፣ የእነርሱ የተፈጥሮ ሥጦታ፥ የጨካኝ ገዢዎቹ መዳሪያ፣ መንደላቀቂያ ሆነ። ወልቃይት እንደ እንክርዳድ፣ እንደ አረም ተለቅሞ፥ ተነቅሎ ተጣለ። "ምርጦቹ" (the Aryans) ተዘሩ፥ ቡቃያው አበበ፥ ሰላሳና ስድሳ መቶ ፍሬ አፈሩ። ታላቁ ሕዝብ ኦሮሞ፥ ተንኳሰሰ፥ ከሚያፈቅረው ቄዬው እንደቆሻሻ ተለቃቅሞ በየጠርዙ ተደፋ፣ ደግሞ ምን ሊያመጣ፣ እያለ፥ ወያኔ ፊንፊኔን በመዳፉ አስገብቶ ተቀናጣ፥ ሞኝ "ጋላ" ብሎ "የሞኞቹን" መሬት ቀምቶ፥ ሲሚንቶ ዘርቶ ሕንፃ አበቀለበት፥ ያውም የጀነራሎቹን፣ ያውም የወያኔዎቹን ቱባ ባለሥልጣናት።

እምበር ተጋዳላይ፥ ኮሎኔል ማራኪ

ጠቅላይ ሚኒስትር አምበርካኪ

ዛሬ ግን ከሃያ አምስት ዓመታት የፋሽዝም አገዛዝ በኋላ፥ ምንም እንኳን ቢረፍድ፥ የጨለማው ድባብ ሊገለጥ መሆኑን የሚያሳዩ የተስፋ ጭላንጭሎች ብልጭ ብልጭ ማለት ጀመሩ። እንደ ኢምንት ፥ በጊንጪ የበረቀው የአንገዛም መብረቅ፣ በነጎድጓድነቱ ድፍን ኦሮሚያን አርዶ፥ ውስጥ ውስጡን እንደ እሳተ ገሞራ እየጋመ፣ በወልቃይት ምክንያት ጎንደር ላይ ነደደ።

ከዚህ በኋላ ኮሎኔል ማራኪ ብሎ መደንፋት ጎንደር ተረት አድርጎታል። ውሾችን (እነ ኃይለማርያምን፥ ሙክታርና፥ ደመቀን) ማንበርከክ ይቻል ይሆናል እንጂ እንደ ኮሎኔል ደመቀ የመሰሰሉትን ሥልጡን ኢትዮጵያውያን እንደማይሞከር ፀሐይ የሞቀው እውነታ ነው።

ከዚህ በኋላ የሚቀረው ሂሳብ ማወራረድ ነው። ዱቼ ሙሶሎኒ ተብሎ እንዳልተዘመረለት፤ የገዛ ሕዝቡ፥ ሙሶሊኒን፥ በአደባባይ ዘቅዝቆ እንዳንጠለጠለው፥ ከአብራኩ ያስገኛችሁ የትግራይ ሕዝብ፣የኦሮሞ ሕዝብ፣የአማራ ሕዝብ በዚያው ሚዛን ዋጋችሁን የሚሰጣችሁ ጊዜ በእርግጥም በሩቅ ሳይሆን በቅርብ ርቀት እያየነው ነው። የመስቀያው ማማ ቆሟል። የአንገትጌው ገመድም በጥሩ ሁኔታ ተሸርቧል የቀረው ወደ መሰቀያው ደርብ የምትወጡበት ቀን ነው (ፍርድ የምትቀበሉበት አግባብ)። የፉኸረሩ መንግሥት፥ የመለስ አገዛዝ፥ እንደ ቀደምት ገናና አምባገነኖች ሁሉ ትቢያ ሊሆን እነሆ ፍርድ ከደጃፍ ቆሟል።

መጽሐፍ **የሆነው ነገር እርሱ የሚሆን ነው፥ የተደረገውም ነገር እርሱ የሚደረግ ነው፤ ከፀሐይም በታች አዲስ ነገር የለም።** ያለው ይፈጸም ዘንድ ግድ ነውና፤ የኤልዛቤልን ደም የላሰው ውሻ (መቅሠፍት) በጣም ቀርቧል፥

ቻው ታላቋ ትግራይ፥ የእነ አርጤምስ ቅዠት፣ ሳትወለጂ በጽንስ የጨነገፍሽ፣ ሻትሞሸረ በምኞት የገለሞትሽ፣ ሳታፈሪ የደረቅሽ፣ ሳታድጊ የተቀጠፍሽ፤ አርጢሚጢጢዮስ (ለአርጤምስነት ያልበቃውን ኃይለማርያምን ለመግለጽ ነው። እርሱ ሊመለክ ያልበቃ፣ በራሱ መቆም ያልቻለ ልምሾ ነውና) አንቺን ሊገነባ፣አንቺን ሊያገንን፥ የገባውን ቃለ መሐላ መፈጸም አልቻለምና። የዱቼው መለስ ቅዠት፥ ታላቋ ትግራይ ሆይ፥ ቻው።

ተስፋዬ